መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



# የእግዚአብሔር መልዕክተኛ

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2015 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ሽማግሌው ካህን ዘካሪያስ በቤተመቅደስ ውስጥ
ዕጣን ያጥን ነበር።ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው
ይጸልዩ ነበር።የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ
ቀኝ ቆሞ ታየው።ዘካርያስም በድንገት
ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት።




መልአኩም እንዲህ አለው፦ ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና
አትፍራ።ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥
ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።ገናም
በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ
ይሞላበታል።



በውጭ ያሉት ሰዎች ዘካሪያስ ዲዳ በመሆኑ
ተገርመዋል። መልዓኩ ገብርኤል በጊዜው
የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፥ ይህ ነገር
እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ
ትሆናለህ መናገርም አትችልም
ያለውን አላወቁም ነበርና።ሚስቴ
ስላረጀች ልጅ መውለድ
አንችልም
ብሎ ነበር።

ዘካሪያስ እግዚአብሔር የተናገረውን
ሁሉ ማስታወሻ ይጽፍ ነበር።ሚስቱ
ኤልሳቤጥ ሁልጊዜ ይገርማት ነበር።
ስለ ልጅ ሁል ጊዜ ይጸልዩ ነበር።





ኤልሳቤጥም
እንደፀነሰች አወቀች።
እግዚአብሔርን
አመሰገነች። ዘመድዋ
ማርያምም አንድ ቀን
ልትጠይቃት ወደ ቤቷ
መጣች። ማርያምም
ፀንሳ ነበር።



ኤልሳቤጥም
የማርያምን ሰላምታ
በሰማች ጊዜ ፅንሱ
በማኅፀንዋ ውስጥ
ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም
መንፈስ ቅዱስ
ሞላባት፥ የማርያም
ልጅ ጌታ ክርስቶስም
እንደሚሆን ታውቅ
ነበር።ሁለቱ ሴቶች
በአንድነት
እግዚአብሔርን
አመሰገኑ።



ኤልሳቤጥም ልጇን ወለደች።
ካህናቱ በአባቱ ስም ዘካርያስ
ሊሉት ወደዱ።እናቱ ግን መልሳ።
አይሆንም፥ ዮሐንስ ይባል እንጂ
አለች። አባቱም ስሙ ዮሐንስ
ነው ብሎ ጻፈ።ያንጊዜም አፉ
ተከፈተ መላሱም ተፈታ
እግዚአብሔርንም
እየባረከ ተናገረ።



ዮሐንስ ሲያድግ ልክ እንደ እግዚአብሔር ሰው ኤልያስ ነበር።የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሊባርካቸው እንደሚመጣ ለሕዝቡ ይናገር ነበር።ንስሐ ግቡ! ከኃጢአታችሁ ተመለሱ! ይላቸው ስለነበር የአይሁድ መሪዎች ዮሐንስን ይጠሉት ነበር።

የንስሐ ጥምቀት ያጠምቃቸው ስለነበር
አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ ብለው
ይጠሩት ነበር። አንድ ቀን ኢየሱስ
በዮሐንስ ሊጠመቅ መጣ።ዮሐንስ
ግን በእኔ አትጠመቅም
አለው። ኢየሱስ ግን
ግድ አለው።
ዮሐንስም
እሺ አለና
አጠመቀው።



ኢየሱስ ወዲያው ከውኃው
በወጣ ጊዜ ሰማያት
ሲቀደዱ መንፈስም እንደ
ርግብ ሲወርድበት አየ።
የምወድህ ልጄ አንተ
ነህ፥በአንተ ደስ ይለኛል
የሚል ድምፅ ከሰማያት
መጣ። ዮሐንስ ኢየሱስ
የዓለምን ኃጢአት
የሚያስወግድ
የእግዚአብሔር በግ
እንደሆነ ያውቃል።



ዮሐንስ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መልሶ ነበር።ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ሄሮድያዳን ስላገባት ዮሐንስ ገስጾት ነበር።



ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደሆነ ሄሮድስ ቢያውቅም ኃጢአቱን መተው ግን አልፈለገም።ዮሐንስም ስለ ጽድቅ መስበኩን አልተወም። በዚህም ምክንያት ይህ አመጸኛ ገዥ ዮሐንስን እስር ቤት ከተተው።

ሄሮድስም በተወለደበት ቀን የሄሮድያዳ ልጅ ገብታ ስትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው።የመንግሥቴ እኩሌታ ስንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት።





ወጥታም ለእናትዋ።
ምን ልለምነው?
አለች። እርስዋም፥
የመጥምቁን
የዮሐንስን ራስ
አለች። ሄሮድያዳ
ዮሐንስን ትጠላው
ነበር።

ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ
ገብታ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ
በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ
ብላ ለመነችው። ንጉሡም እጅግ
አዝኖ ስለ መሐላው ስለ ክብሩ ሲል
ሊከለክላት አልወደደም።ወዲያውም
ንጉሡ ወታደሩን ልኮ
ራሱን እንዲያመጣ
አዘዘው። ሄዶም
በወኅኒ ራሱን
ቈረጠ።



ደቀ መዛሙርቱም
ሰምተው መጡ የጻድቁንና
የታማኙን አገልጋይ በድን
ወሰደው ቀበሩት። ዮሐንስ
ተልዕኮውን ፈጽሞ ሄዷል።
ኢየሱስም ከሀዘናቸው
እንደሚያጽናናቸው
ደቀመዛሙርቱ
ሳያስቡ አልቀረም።



የእግዚአብሔር መልዕክተኛ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማርቆስ ወንጌል 6
እና የሉቃስ ወንጌል 1 እና 3

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! ዮሐ. 3.16